ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (KNAASO)
766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

---

ሜይ 9 2008

# ሉዓላዊነታችን ለድርድር አይቀርብም

የኢትዮጵያ ድንበርና ሉአላዊነት ተጠብቆና ተከብሮ ከጥንት ጀምሮ አባቶቻችን አጥንታቸውን ከስክሰውና ደማቸውን አፍስሰው ለተከታዮቹ ትውልዶች እንዲተላለፍ አድርገዋል። በጊዜው ከነበሩት ነገሥታትም ሆነ አስተዳዳሪዎች ሥር በመሰባሰብ እኔ ከዚህኛው ወገን ነኝ፤ እኔ ከዚህኛው ክልል ነኝ ሳይሉ ድንበራችንን የደፈረውን ሁሉ በጠላትነት በመፈረጅ ቤቴንና ቤተሰቤን ሳይሉ በአንድነት በመሰለፍ እናት ኢትዮጵያን የታሪክ ቀንድ አድርገዋት በዓለም ዙሪያ ባንዲራዋ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ፣ ሉዓላዊነቷ በመላው ዓለም ታውቆ እንድትኖር፤ ክብርዋ ገንኖ እንዲሰማ በማድረግ አቆይተውናል።

የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት የወቅቱን ትውልድ ድንብርህ ተነካ ብሎ ድንበሩን ከወራሪ እንዲከላከል በጠራው ጊዜ የኢትዮጵያ ድንበር በእኛ ዘመን ሊደፈር አይገባም በማለት ተነሥቶ ያስገኘው ድል ለኢትዮጵያ መጥፎ አሳቢዎች ትምህርት የሰጠ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎችም ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት ውድ ለሆነችው አገራችን ድንበርና ክብር ሲሉ ነው።

ይህ የደምና የአጥንት ውርስ ሊደፈርም ሆነ አጠያያቂ ሆኖ የተገኘው በወያኔ ኢህአዴግ ሥርዓተ መንግሥት ጊዜ ብቻ ነው።

ከሰሞኑ በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው ሥልጣኑን በመሣሪያ አፈሙዝ ተቆጣጥሮ የሚገኘው የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት ወገኖቻችንን ከሀገራቸውና ከቀያቸው በማፈናቀል አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን ከሁመራ እስከ ጋምቤላ የሚሸፍነውን ለም የኢትዮጵያ መሬት ከሱዳን መንግሥት ጋር ባደረገው ስምምነት አሳልፎ መስጠቱን ከተለያዩ ዜና ማሰራጪያዎችና ከአካባቢው እማኞች በተገኘው መረጃ መሠረት ይፋ ሆኗል። በሌላም በኩል ይህን ውሳኔ ለማስፈጸም ድንበር ዘልቆ የገባው የሱዳን ታጣቂ ኃይል የአያሌ የአካባቢው ነዋሪዎችን ቤቶችና ንብረቶች በእሳት እንዲወድም አድርጓል። ይህ ድንበር ዘልቆ የገባው የሱዳን ኃይልም በአካባቢው እንዲሰፍር ተደርጎ ጭካኔ የተሞላው በደል ከመፈጸሙም በላይ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎችን በማገት የት እንዳደረሷቸውም አይታወቅም።

በአገሩ የሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ መወሰን ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ እያለ የመለስ ዜናዊ መንግሥት ግን ዳር ድንበሩና መሬቱ በሱዳን እንዲደፈር ሲፈቅድ የሕዝብ እንደራሴ ተብዬዎችም የመረጡት ዝምታን ነው። የሱዳን የታጠቀው ኃይል ዳር ድንበራችንን ደፍሮ ጥሶ በመግባት በአካበቢው ኢትዮጵያኖች ላይ ጥቃት ሲያደርስ አሁንም የአገራቱ የመከላከያና የደኅንነት ኃይል ተብዬውም በዝምታ እየተመለከተ ነው።

ስለሆነም እኛ በሰሜን አሜሪካን በቅንጅት የድጋፍ ሰጪ ማህበር ሥር ተደራጅተን የምንገኝ ወገኖች ከዚህ በታች ለተመለከቱት የመግሥትና የሕዝብ ኃይሎች የሚከተሉትን ጥሪዎች ስናስተላለፍ ለሉአላዊነታችን መከበርና የሕዝብ አለኝ ታነታችንን በማጠናከር ነው።

## ለኢትዮጵያ ሕዝብና የዲሞክራሲ ኃይሎች

በፍትሕና በእኩልነት መንፈስ ለቆማችሁ የዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር በሚደረገው እንቅስቃሴዎች በአንድ ላይ በመቆም ትግላችንን እንድናጠናክር ጥሪያችንን ስናቀርብ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለሚቀርብለት የትግል ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ እንደሚሰጥ በመተማመን ነው።

## ለሱዳን መንግሥትና ሕዝብ

ድንበራችንን ደፍሮ በመግባት የከተመው የአገራችሁ የታጠቀ ኃይል በአስቸኳይ ከግዛታችን ሠራዊቱን እንዲያወጣ ስንጠይቃችሁ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውቅና ውጭ ሉዓላዊነትን አስመልክቶ የሚደረግ ማንኛውም ስምምነት ሕገ ወጥና በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የሚያስከትለው መዘዝ አደገኛ መሆኑን ከወዲሁ በማመላከት ነው።

## የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊትና የደህንነት አባላት በሙሉ

ትናንት በሰሜኑ የአገራችን ክልል ሉዓላዊነታችን ተደፍሮ መሬታችን በመያዙ ደምህን አፍስህ አጥንትህን ከስክሰህ ያስከበርከውን ዳር ድንበር መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ለከፈልከው መስዋዕትነት ዋጋ ባለመስጠት በደምህ ላይ እየተደራደሩ ይገኛሉ። እንዲሁም በቅርቡ አቶ መለስ ዜናዊ በማይመለከተው የሱማሊያ ሕዝብ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ በመግባት አላስፈላጊ መስዋትነት በመክፈል ላይ ነህ። አሁን ደግሞ ለዘመናት ተከብሮ የቆየ መሬትህ ለሱዳን መንግሥት ሲሰጥ በዝምታ መመልከትህ ከከሀዲዎችና ከአገር ሻጮች ጎራ መሰለፍህን የሚያረጋግጥ ነው። ስለዚህ ለዘለቄታው የምንደኛው የመለስ ዜናዊ ሰለባ ሆነህ እንዳትቀር ከሕዝብ ጎን ተሰልፈህ የአገርህን ግዛት እንድታስከብር እናስገነዝባለን።

## ለፓርላማ አባላት

የአገር ሉዓላዊነትን በሚመለከት ሕዝብን ወክሎ የመምከርና የመወሰን ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን የእናንተ ሆኖ ሳለ ከበስተጀርባችሁ ወያኔ ኢህአዴግ በአገር ሉዓላዊነት ዙሪያ ሲደራደር በዝምታ መመልከታችሁ ነገ በታሪክና በሕዝብ ዘንድ እንደሚያጠይቃችሁ ተረድታችሁ ዝምታችሁን በመስበር ሉዓላዊነቱን ከማያስደፍረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንድትሠለፉ እናስገነዝባለን።

የኢትዮጵያ ዳር ድንበር አሁንም ወደፊትም በጀግኖች ልጆችዋ ለዘላለም ተከብሮ ይኖራል።

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማህበር